


## ሚዛኑ አየለ   ጀርመን - ፍራንክፈርት

# ይድረስ ለጥንት ጓደኛዬ!!!

የ 27 አመት ጓደኝነታችን ብዙ ትዝታዎችና ገጠመኞችን ያካተተ እንደሆነ ትስተዋለህ ብየ አልገምትም ፣ ከበጎ ትዝታዎች

በተለይ የማስታዉሰዉ ሚንስክ- ቤላሩስያ ይማር ለነበረዉ ጓድኞችን ሚዜ ስልነበርን አንተ ከታሽኬንት - ኡዝቤኪስታን አኔ ደግሞ ከሞስኮ - ሩሲያ በተማሪ አቅማችን ኢትዮጵያ ድረስ በመሂድ ያደረግነዉ የምላሽ ግብዣ ነዉ ፣ በተለይ አንተ በጣም ተጫዋችና መዝናናትን የምትሻ ወጣት ስለነበርክ በሁሉም ጓደኞቻቸን የነበረህን ተወዳጂነት አስካሁን አስታዉሳለሁ ።

ባላሰብነዉ ሁኔታ በስድት ብንኖርም የጌታ ፈቃድ ሆኖ እንደገና መገናኘት ብቻ ሳይሆን ጎረቤትም ሆነናል ፣ በዚህም ደስተኛ ነኝ፣

በስራ ጸባያችን ምክንያት የጊዜ እጥረት ቢኖርም  አልፎ አልፎ እንድንጠያየቅ አስችሎናል ። ባለፉት 3 ወራት ከአንዴም ሁለቴ

ቤትህ ድረስ በመጣሁ ጊዜ ስላሳለፍነዉ የወጣትነት ዘመናችንና ስለሃገራችን በሰፊዉ ተወያይተናል ፣ በግል እንደ ወንድም ስለራሴ ፣ ስለ ቤተሰቤና በተለይም ስለ ልጆቼ ለሰጠሽኝ ምክር ከልብ አመሰግናለሁ ፣ በሃገራችን የፖለቲካ ዙሪያ ያለን ልዩነት ግን

ከጊዜ ወደ ጊዜ ስር እየሰደደና እየሰፋ እንደሄደም ለመገንዘብ ችያለሁ።

ዉድ ጓደኛዬ፣

ከ18 አመት በፊት ሁለታችንም የአንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት አባላት እንደነበርን መቸም አትዘነጋውም፣ ያለንን ዕዉቀትና ጉልበት አቀናጅተን አብዛኛዉን የጀርመን ዳያስፖራ ለማሰባሰብ በመቻላችን ከአሜሪካና ከሌላም አካባቢ የሚጎበኙን አለቆቻችን

የልብ ልብ ስለተሰማቸዉ ከዉስጣችን በነበሩ ግልፍተኞች እየታገዙ በመንግስት ላይ ጦርነት እንከፍታለን ብለዉ አርፉት፣

ለዚህ ጀብደኛ ስሜት አብዛኛዉ እጁን ባወጣ ጊዜ በኋላ ደጋፊዎቼ እየበረከቱ ቢሄዱም በወቅቱ እኔ ብቻ ነበርኩ ይህን አጥፊ ዉሳኔ

አጥብቄ የተቃወምኩት፣  በጊዜዉ ለወሰድኩት አቋም  ምክንያት የሆኑኝን 3 መሰረታዊ ነጥቦች በማንሳትም አስረድቻለሁ ፣ ለማስታወስ ያህል፡

1ኛ/  17ቱ የደርግ ዘመን ጦርነት የሚሊዮን ዜጎችን ህይዎት ሰለባ በማድረግና በገንዘብ ሊተመን የማይችል ቁሳዊ ጉዳት ከማድረሱ ሌላ ለሰላም ያበረከተዉ አንድም አስተዋጽኦ ባለመኖሩ,

2ኛ/ ጦርነት እንደመጨረሻ አማራጭ የሚወሰድ ከሆነም ከዚያ በፊት ማለፍ የሚገባን ሰላማዊ የትግል እንቅስቃሴ ስላልተደረገና፣

3ኛ/  በሆነዉ መንገድ  ይሁን የፖለቲካ ልዩነታችንን በዉይይት ከመፍታት ዉጪ ባዕድ አስካልወረረን ድረስ በሃገሬ ላይ ምንም አይነት ጦርነት አልደግፍም፣ አልሳተፍም የሚሉት ሲሆኑ በጊዜዉ ከየአቅጣጫዉ የደረሰብኝን ወከባ ከራስህ ግንዛቤ አንጻር ነግረሽኛል ፣ ዉጤቱም እንዳስረዳሁትና እንደተነበይኩት ነዉ የሆነዉ ፣ ከየዋሆች የተሰበሰበዉን ገንዘብ አለቆቻችን አዉሮፓና አሜሪካን ጎበኙበት ፣ ሱዳንና ግብጽ በመሄድ ተዝናኑበት ፣ ቀሪዉን ኬንያ ለነበሩ የደርግ መኮንኖች ማለት ለጓደኞቻቸዉ አስረክበዉ ተመለሱ ፣ ሌላዉ ቀርቶ የመኮንኖች  መጨረሻም አላማረም ፣ በተባራሪ እንደሰማሁት ምግብ ቤት በመክፈትና ታክሲ በመግዛት ከወጣት ኮረዳዎች ጋር ዓለማቸውን ሲቀጩ ቀሳፊዉ ቅጭቷቸዋል ነዉ የሚባለዉ ፣ አንድም የተረፈ የለም።

እኔን በተመለከተ ይፋ በሆነ ስብሰባ ላይ የማምንበትን በመናገሬ ብቻ የደረሰብኝን እንደገና ላስታዉስህ፣

ይፓርቲዉ ስራ ኣመራር በፍራንክፉርት ወጣቶች ማዕከል አዳራሽ የ2 ቀን ዝግ ስብሰባ ኣድርጎ ነበር ፣ አዳር አዚያዉ ነዉ ፣ እኔና ጓደኛዬ በነበርንበት ክፍል የሚተኙ ተሳታፊዎች እኛን እንዲከታተሉ መመድባቸውን ያወቅነዉ በኋላ ነዉ፣ ሌሊት ጭልጥ ያለ እንቅልፍ እንደወሰደን ቀደም ሲል በወሰኑት መሰረት ለድርጅቱ የደህንነት ሃላፊዎች ከዉስጥ ሆነዉ ይከፍቱላቸዉና ሻንጣችንን ምንቅርቅር ኣድርገዉ በመበዝበር ፈትሸዉ ይወጣሉ ፣ በማግስቱ ቁርስ ላይ በደርግ አገዛዝ በሱዳን የኢትዮጵያ ኤምባሲ የጸጥታ ሃላፊ ነበርኩ የሚል ግለሰብ አጠገቤ ይመጣና „ በቦን የተደረገዉ ስብሰባ እንዴት ነበር „ ብሎ ይጠይቀኛል ፣ እኔም ከስብሰባችን ጋር ምንም ግንኙነት የሌለዉ ጉዳይ ስላነሳብኝ ትንሽ ግር ቢለኝም „ በጣም ጥሩ ነበር፣ ከሁሉም በላይ የዳያስፖራዉ ብሄራዊ ስሜት በጉሉህ የታየበት ነበር“ በማለት መለስኩለት ፣ የጥያቄዉ መነሻ ሻዕቢያ በከፈተብን ጦርነት ምክንያት ኤምባሲያችን ለዜጎች ባደረገዉ ጥሪ ላይ ተገኝቼ አጋርነቴን ለመግለጽ የከፈልኩት የ100 ጀርመን ማርክ ደረሰኝ በሌሊቱ ፍተሻ ወቅት ስለተገኘብኝ እንደሆነ የገባኝ በጣም ዘግይቶ ነው ። እንዲያዉም የሻዕቢያ ጦር አዉሮፕላን ምንም የማያዉቁ ህጻናትን ትምህርት ገበታ ላይ እንዳሉ የቦንብ ናዳ ስላወረደባቸዉ መንግስት ለሚወስደዉ ዓጻፋ ያለኝን ሙሉ ድጋፍ በጽሁፍ ሳይቀር ገልጨ ነበር ፣ ይህን አላገኙትም፣ አላዩትም ።

አዉሮፓ መኖሬ በጀኝ እንጂ አቅማቸው ፈቅዶ በሚቆጣጠሩት ክልል ብሆን ምን ሊያደርጉኝ እንዳሰቡና እንደሚችሉ ሳስብ የፖለቲካ ባህላችን አሁንም የተለያዩ አመለካከት ለማስተናገድ አለመቻሉ እጅግ ያሳዝነኛል ፣ ከዚያ ወዲህ „ ክተት“ ተብሎ የታወጀውን ጦርነት የተከተሉ የት እንደደረሱ አይታወቅም ፣ በዚያዉ እንደወጣሁ ነዉ የቅረሁት ፣ ያ ዉሳኔ „ ስህተት“ እንደነበር የነገርከኝ ድርጁቱ እንደ ጉም መንምኖ ከጠፋ በኋላ ነዉ-።

## ዉድ ጓደኛዬ

አንተ እንዳልከዉ „ ዓየር ባየርም “ ሆነ በነጻ ገበያ ኤኮኖሚ ሃገራችን በዕድገት ጎዳና ላይ እንደሆነች ተግባብተናል፣ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ፍጹም አሳምኖኛል ፣ ለኔ ከኤኮኖሚያዊ ጠቀሜታዉ እጅግ በላቀ የሚታየኝ ለብሄራዊ ሉዓላዊነታችን ያለዉ አንድምታ ነዉ ፣ ዓጼ ዮሐንስ መተማ ላይ ምስዋዕት የሆኑት ፣ ዐጼ ቴዎድሮስ መቅደላ ላይ የወደቁት ለአባይ ነው ፣ እነኝህ እውቅ መሪወቻችን ሃገር ምን ማለት እንደሆነ ምትክ የሌለው ህይዎታቸውን በመስጠት ለተከታዩ ትውልድ ህያው የሆነ ትምህርትና አደራ ሰጥተውን ቢያልፉም ከ 140 አመታት በኋላ መለስ ናቸው ኢትዮጵያችንን የለወጧት ከወደቀችበት ያነሷት ፣ከተረሳችበት ያስታወሷት ፣ የሚታይ የሚጨበጥና የሚዳሰስ ስለሆነ ማስተባበል አይቻልም፣ በተለይ የህዳሴዉ ግድብ ግንባታ ፣ እንደዚህም ስልህ

የሚታዩ ችግሮችን በማቃለል ወይም በመካድ ኣይደለም፣ ካለፈዉ የተወረሱና አስካሁን የሚንከባለሉ አንዲሁም በሂደት ያጋጠሙ ሰዉ ሰራሽና ጊዜ የሚጠይቁ እንዳሉ ግልጽ ነዉ፣ ግን እስኪ ሁኔታዉን በጥሞና ተመልከተዉ፣

ከ2ሚሊዮን ዳያስፖራ ዕፍኝ የማይሞላ ግሩፕ

_ በዓለም አቀፍ ተቋማትና ኤምባሲ ቢሮ በመለገብ ሃገራችን ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ምንም ዓይነት እርዳታና ብድር እንዳታገኝ

እየተቃወመ፣

_ ለቤተሰብ መደጎሚያ የሚልኩትን ገንዘብ ሳይቀር ብሄራዊ ጠቀሜታ ባለዉ ህጋዊ የሃዋላ መንገድ ሳይሆን በጥቁር ገበያ እየቸበቸበ፣

_- የኤኮኖሚ ፋይዳዉን ሳንጨምር በአፍሪካዉያን ቅኝ ተገዥነት የጨለማ ዘመን የነጻነት ተስፋና ምልክት የነበረዉና , አሁንም የአህጉሪቱ መመኪያ በሆነዉ አየር መንገዳችን አንድም ኢትዮጵያዊ እንዳይጓዝ በአደባባይ እየለፈፈ.

- ከተወሰኑ የተፈጥሮ ሃብት ምርቶች ማለትም ከቡና ወርቅና ጥራጥሬ ሌላ ይህ ነዉ የማይባል የዉጭ ምንዛሬ ምንጭ የሌላት ሃገራችን አሁን ካለችበት በላይ የት እንድትደርስ ነዉ የተፈለገዉ! እስኪ ንገረኝ! ለፖለቲካ መቀራረብ ቅን ልቡና ችሎታና ከሁሉም በላይ ደግሞ በህዝቡ የአስተሳሰብ ደረጃ ተመስርቶ ወደ መቻቻል የሚያመራ መሆን አለበት እላለሁ፣
  መልስህ „ ስልጣን ለጽንፈኛ ካልተሰጠ“ የሚል ከሆነ „ በዓይኔ ልሳቅ እንጂ ጥርሴስ ልማጹ ነዉ „ ብዬ አልፈዋለሁ.
  90 ሚሊዮን ህዝብ በማገልገል ላይ ያለ መንግስት በፈታኝ ጊዜ ህዝቡን ለወሮ በላ አሳልፎ ይሰጣል ብዬ አላምንም፣ አላስብምም፣ አይሆንምም።
  አክራሪዉ ዳያስፖራ እስካሁን ያደረገው መጠን አልባ የጥፋት ተልዕኮ ጣሪያ ደርሶ በልዕለ ሃያላን ሃገር የሚዉብለበለበዉን ክቡር ብሄራዊ ሰንደቅ አላማ እንደ እናቱ መቅነት ፈቶ በማዉረድ ትክክለኛ ማንነቱን አሳይቷል፣
  ይህ ብሄራዊ ወንጀል ጣሊያን አዲስ አበባን በያዘ ጊዜ ከሆነዉ በዕጅጉ የላቀ አሳፋሪ ድርጊት ነዉ፣ ያኔ „ አሻፈረኝ“ በማለት በረሃ እንደገቡ ጀግኖቻችን ሁሉ የመላዉ ዜጋችን ጉጉት ዕንኝህን ወንጀለኞች መፋረድ ነዉ፣ የፈለገዉን ያህል ጊዜ ይዉሰድ ኢትዮጵያን የሚጠብቅ አያንቀላፋም።

  አሳምረህ እንደምታዉቀዉ ኢሳትንም ሆነ ግንቦት 7ትን የፈጠሩት ወገኖች ከሃገር ፍቅር በመነጨ ስሜት ሳይሆን በ ዕልህ፣ጥላቻና በቀል ላይ ተመስርተዉ ነዉ፣„ ፖለቲካ“ የሚሉት ከሽፋን ያለፈ አይደለም፣ እንዲያዉም መነሻቸዉ የ 1997ቱ ምርጫ እንደሆነ አንተም እኔም እንዘነጋዉም።ማጋነን አይሁንብኝ እንጂ መንግስት ለብዙሃን ፓርቲና ህዝባዊ አስተያየት የነበረዉ ትልቅ ፍላጎት ከዚያ በፊት ገና ኢህዴግ ስልጣን እንደያዘ ነዉ በተግባር ማሳየት የጀመረዉ፣ ለመሆኑ ፕሮፌሰር መስፍንና መለስ ዜናዊ እንዲሁም ሌሎች በ ኢቲቪ ያደረጉትን ግልጽ ዉይይትና ክርክር ታስታዉሳለህ! ያ አይነቱ ሃገራዊ ዕሰጥ-አገባ በ 97ቱ ምርጫ ለሁሉም ፓርቲ ተመጣጣኝ ጊዜ ተመድቦለት „ ይበል“ በሚያሰኝ ሁነታ ነበር የተካሄደዉ፣ዉጤቱን አመድ አደረጉት እንጂ፣ ለመሆኑ የዚያ አይነት መድረክ ኢሳት ላይ አይተሃል!፣ ተከታትለሃል!፣ አይሆንም፣ አይታሰብም፣ ግፋ ቢል የከዳ፣ የተባረረ፣ ወይም የኮበለለ፣ ባጭሩ ቢጤያቸዉን እየሰበሰቡ ነዉ የሚያደናግሩን።

ዉድ ጓደኛዬ

እኔ ካንተ ጋር ያኔ ካደረግኩት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ዉጪ ከዚያ ወዲህ በየትኛዉም ድርጅት የለሁበትም፣ የሚገርምህ ነገር ልግባ ብል እንኳ ባሁኑ ወቅት ከነድክመቱ ከ ኢህአዴግ የተሻለ ይኖራል ብዬ አላምንም ፣ እድሜዬ እየገፋ በመሄዱና ያለኝን ግለሰባዊ

ነጻነት በፓርቲ- ፖለቲካ ዲስፕሊን ለማስገዛት ሲለሚያዳግተኝ እንጂ ሌሎች ከዛሬ ጀምሮ እኔም „ አንዳርጋችዉ ነኝ“ እንዳሉት እኔም „ አኢህዴግ ነኝ“ ማለት ፈጽሞ አይከብደኝም። አንዳርጋቸዉን ካነሳሁ ላይቀር አንድ ነጥብ ልጨምር፣

የግለሰቡ ዕጣ- ፋንታ እንደማንኛዉም ሰብዓዊ ፍጡር ያሳዝነኛል፣ ለደረሰበትና ላለበት ሁኔታ ግን ተጠያቂዎች እራሱና ድርጅቱ ብቻ ናቸዉ፣ ሌላ ማንም አይደለም። „ የሞተ ሰዉ አንገተ-ረጅም ነዉ“ እንደሚባለዉ ዛሬ በኢሳትና ሌሎች ግብዞች የምንሰማዉ የሱን „ ጻድቅነት“ ሲሆን ዕዉነቱ ግን ፍጹም ተቃራኒዉ እንደሆነ በመለስ ህልፈተ- ህይዎት ጊዜ ያለዉን እናስታዉሳለን፣ የሞተ ሰዉ ሳይቀር  ይቅርታ ማድረግ የማይችል ጨካኝ ነዉ፣ የተናገረዉን ቃል በቃል ባስታዉሰውም  እዚህ ላይ አልደግመዉም፣ ለማገናዘብ እንዲረዳህ እነ ሰዬ አብርሃና ብርቱካን ሚደቅሳ ካሉት ጋር አነጻጽረዉ፣ ሰዉዬዉ በጥላቻ ከመታወሩ የተነሳ በሬሳ ላይ የደነሰ ፣ ሞራልና ዕሴት የጎደለዉ ፍጡር ነዉ፣ የሚለዉ ብቻ ነዉ ትክክለኛ ማንነቱን የሚገልጸዉ። ታዲያ ዛሬ በተለያዩ የአዉሮፓና አሜሪካ

ከተሞች በየሳምንቱ የሚወጣለት „ የሰልፍ ተዝካር „ ገነት ሊያስገባዉ ቀርቶ ካለበትም አያወጣዉም፣ የዓለቃዉን ተራ ከማፋጠን

ባለፈ ምንም ሊፈይድ እንደማይችል የጥቅም ጉዳይ ሆኖ እንጂ ኢሳትም ኣሳምሮ ያዉቃል።

ዉድ ጓደኛዬ

ባለፈዉ ሰሞን የመንን ለሁለት ዙር በጠቅላይ ሚንስትርነት ያገለገሉትንና የ „ ማድሪድ ክለብ“ አባል የሆኑትን ዶ/ር አብዱልከሪም

አሌርያኒን የማግኘት ዕድል አግኝቼ ነበር፣ ክቡርነታቸዉ ከመከሩኝ ጥቂቱን በግርድፉ ላካፍልህ፣

„ ኢትዮጵያውያን ፊታችሁ ላይ ካፈጠጠዉ ዕውነታ በይበልጥ ለታሪካችሁ ነዉ ትልቅ ዋጋ የምትሰጡት፣ ሁላችንም የሳባ ልጆች ስለሆን ለዚህ አመለካከታችሁ ክብር ቢኖረኝም ዛሬና ነገን በአግባቡ የማየት ችግር ያለባችሁ ይመስለኛል፣በጎውን ቢቻ በማሞካሸት

ተወስነን ካለፈዉ መማር እስካልቻልን ድረስ ታሪካችን በጽሁፍና ቅርጻ-ቅርጽ ከመታየት ባለፈ የህዝቡን ኑሮ የሚለዉጥ አይደለም፣

እኛ እስካሁን በባህላዊዉ የአካባቢ ነገድ የምንተዳደር አንድ ህዝብ እንጂ እንደ እናንተ የብሄርና ብሄረ-ሰቦች ባለጸጋ አይደለንም፣

ሆኖም ወደ 20 ፐርሰንት የሚሆነዉ ህዝባችን የሺኢት እምነት ተከታይ በመሆኑ ብቻ ያለብንን ችግር በየቀኑ የምታየዉ ነዉ፣

ልነግርህ የምፈልገዉ ለብሄራዊ አንድነት እስካሁን ባለዉ የመስተዳድር ዘይቤ ብቸኛዉ መፍትሄ ፌዴራላዊ ሲስተም መሆኑን ነዉ፣

ስለዚህም ይህን አማራጭ ለመጠቀም በከፍተኛ ጥናት ላይ ነን፣ ጀርመን እንድመጣ ካደረጉኝ ምክንያቶች አንዱና ዋናዉ እሱ ነዉ፣

ለነገሩ አንተ እዚህ እየኖርክ ያለዉን ጠቀሜታ በሚገባ ታዉቀዋለህ ብዬ እገምታለሁ። እናንተ ጅምራችሁ ጥሩ ሆኖ ሳለ ያጋጠሙ ችግሮች  በሂደት እየታዩ እንዲስተካከሉና የጎደለዉ እንዲሟላ ከመንግስታችሁ ጋር በመመካከር አስፈላጊዉን ድጋፍ በማድረግ የጎደለው እንዲታረም

ማድረግ ሲጠበቅባችሁ ሁሉንም አሻፈረኝ በማለት በየክፍለ-ዓለሙ መሽጋችሁ የሃገራችሁን ክብር እየቀነሳችሁ መሆኑ ሳያንሳችሁ ድንበር ኣልፋችሁ በኛ ላይም እየተንጫጫችሁ ነዉ። ታስታዉሳለህ! በ 1976- 77 ሶማሊያ ድንበራችሁን ጥሳ እስከ 700 ኪሎ ሜትር በመግባት በወረረቻችሁ ጊዜ ግብጽ፣ ሱዳንና ሌሎች አረቦች መጠን የሌለዉ የገንዘብና የመሳሪያ ድጋፍ ለሞቃዲሾ ሲያጎርፉ ፣ የራሽያ መሳሪያና የኩባ ጦር ሳይደርስ ቀብሪደሃርና ቀላፎ ላይ ለዚያድባሬ ጦር ደረቱን የሰጠዉ የኛ መድፈኛ ብርጌድ ነበር፣ እረሳችሁት ማለት ነዉ! አረ እየተስተዋለ! ከቋንቋና እምነታችን በመለስ ሁሉ ነገራችን ከእናንተ ጋር አንድ ነዉ፣ ሁላችንም የሳባ ልጆች ለመሆናችን ማረጋገጫ ነዉ፣ ሌላዉ ልነግርህ የምፈልገዉ እንደምታየዉ ዓለማችን ከምንገምተዉ በላይ በሆነ ፍጥነት እየተለዋወጠ ስለሆነ ከጊዜዉ ጋር አብሮ መጓዝ ካልተቻለ ኋላ መቅረትን ያስከትላል፣ ሃገራችሁ ታላቅና ጥንታዊ ናት፣ ግን ያለፈዉን ብቻ ማሞካሸት ያሁኑን ዕዉነታ ይገልጻል ብዬ አላምንም፣ ወደፊትም ባለፈዉ መቀጠል አይቻልም፣ ቱርክን ስፔይንን ኢንግላንድንና ለሎችንም ማየት ትችላለህ፣ ለረጅም ዘመናት ዓለማችን በእጅ መዳፋቸዉ እንዳልነበረች ዛሬ ሁሉም የአንድ ሃገር መንግስት ታዛዥ ናቸዉ፣ የ አሜሪካ!፣ በመሆኑም ባትፈልገዉ ዕንኳ መጋፈጥ የማትችለዉ ከሆነ ራስህን ዝቅ ኣድርገህ ማሳለፍ ተገቢና ብልህነት ይመስለኛል፣ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ገና ዳዴ የሚል ይቅርና አድገናል፣ ተመንድገናል፣ የሚሉትም ከዋሽንግቶን ትዕዛዝ አያልፉም፣ እንዲያዉም በዚህ ረገድ ከአንዳንድ የአዉሮፓ ሃገሮች ይልቅ ተሰሚነት እያገኘች የመጣችዉ ሃገራችሁ ናት ፣ በአፍሪካ ግብጽ የነበራትን ቦታ አስለቅቃታለች ፣ የአካባቢዉን ሰላምና ደህንነት ትመራለች፣ ታስተባብራለች፣ ባጭሩ ያላችሁ ተሰሚነት ጨምሯል፣ አድጓል ፣ የሁለቱ ሶማሌዎችና ሱዳኖች ዕጣ- ፋንታ በእናንተ ትክሻ ላይ ነዉ የወደቀዉ፣ ልብ በል! የምዕራባዉያንን ድጋፍ የምታገኙት ጠንካራ እስከሆናችሁ ድረስ ብቻ ነዉ።

አንድ በጣም አጭር ምሳሌ ልንገርህ፣ ከ 6 አመት በፊት አሜሪካ የዓየር ክልላችንን በመጣስ አልቃይዳ የሚባለዉን አሸባሪ ቡድን በሰዉ አልባ በራሪ ስትደበድብ ነጻ ሃገር እንደመሆናችን ልትጠይቅንና ልታስፈቅደን ይገባ ነበር፣ አላደረገችዉም ፣ ማለት ከምንም አልቆጠረችንም፣ በመጨረሻ ያደረግነዉ ምን እንደሆነ ታዉቃለህ! እኛ እራሳችን ጠይቀን የጀመረችዉን እንድትቀጥል ፈቀድንላት፣ አካሄዳቸዉን ታዉቃለህ፣ ይህን ባናደርግ የሚደረግልን ዕርዳታ ሁሉ ይቋረጣል፣ ከዚህ የባሰዉና አደገኛዉ ሁኔታ ደግሞ መንግስታችን እንዳለ ከአሸባሪዎች ጎን ሊፈረጅም ይችላል፣ መጀመሪያ አሸባሪዎችን በበቂ ሁኔታ አይከላከልም ትባላለህ፣ ቀጥሎ ጥግ ይሰጣል የሚለዉ ይከተላል ፣ በመጨረሻም እራስህ አሸባሪ ሆነህ ትፈረጅና ጥቁር መዝገብ ዉስጥ ትገባለህ፣ ከዚያ በኋላ ምንም ዋጋ የለህም፣ የመርገም ጨርቅ ነህ ። ለዚህም ነው በሌለን አቅም ጭራሽ ከማንችለዉ ሃይል ጋር ከምንጋፈጥ በፈቃደኝነት ይሻላል ብለን እጃችንን የሰጠነዉ፣ ከየትኛዉ ወገን እንደሆንክ ባላዉቅም ካለኝ ልምድና ተመክሮ በመነሳት ነዉ የግል አስተያየቴን ያካፈልኩህ „ ብለዉኝ ተለያየን።

በፕሬዚደንት ሳልቫኬርና ዶክተር ማቻር መካከል ባለው የስልጣን ግብግብ ዘብጥያ የወረዱትና ከተፈቱ በኋላ በተደራዳሪነት

አዲስ አበባ ያገኘኋቸዉ የቀድሞዉ የደቡብ ሱዳን የባህልና ወጣቶች ጉዳይ ሚንስትር ዶክተር ሲሪኖ ሂተንግ የነገሩኝም ፍጹም ተመሳሳይ ነው፣ „ ያለ ኢትዮጵያ ሁለ-ገብ ድጋፍ ከመጀመሪያዉ ነጻነታችንን አናገኝም ነበር ወደፊትም ያለ ኢትዮጵያ ህልዉናችን

ዋስትና የለዉም።“ ነው ያሉኝ።

ሀገራችን ያለችበትን የዕድገት ደረጃ በተመለከተ ፕሬዚደንት ኦባማ በቅርቡ የኢትዮጵያን ከፍተኛ ልዑካን ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት ,“ ኢትዮጵያ በዓለማችን ፈጣን የኤኮኖሚ ዕድገት በማስመዝገብ ላይ ከሚገኙ ሃገሮች አንዷ ናት፣

በአንድ ወቅት ህዝቧን ለመመገብ የተሳናት ሃገራችሁ ዛሬ በግብርና ውጤት ብቻ ሳይሆን የሃይል ምንጭ ለውጭ ገበያ እያቀረበች ነዉ፣ አውሮፕላናችንን በመግዛት ለአሜሪካውያን ሳይቀር የስራ ዕድል ፈጥራለች፣ በዲስፕሊን የታነጸው ጠንካራ የመከላከያ ሃይሏ

ሽብርተኝነትን በመዋጋትና ሰላም በማስከበር የምታበረክተው ድ ርሻ በአፍሪካና በመላው ዓለም ተሰሚነቷን አጉልቶታል „ በማለት ነው ዕውነቱን አጠርና ምጥን ባለ አጭር ኣገላለጽ ያስቀመጡት። ያለማጋነን ኢትዮጵያችን እንዳሁኑ ተሰሚነቷ የጨመረበትና ክብሯ የገነነበት አንድም የታሪክ አጋጣሚ የለም፣ የበፊቱ አንድም ለንጉሱ ወይም ለጥንታዊነቷ ነበር።

ዉድ ጓደኛዬ

ሰንደቅ አላማችን ያዉ የምናዉቀዉ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ነዉ፣ አልተለወጠም አልተቀነሰም አልተጨመረም፣ በንጉሱ ጊዜ መስቀል ከዘዉድ ጋር የተሸከመ አንበሳ ተለጥፎበት ነበር፣ በደርግ ደግሞ ሞፈርና ቀንበር፣ እንዲሁም ኮከብና ማጭድ ዎይም የአክሱም ሃዉልት ወዘተ፣ አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ለሃገራችን ይበጃል ብሎ የፌዴራል መዋቅር ስለዘረጋ ክልሎችን የሚያገናኝ፣ አላማቸውንና አንድነታቸዉን የሚያመለክት የጋርዮሽና አብሮነት ምልክት የሆነ ብሩህ ኮከብ አድርጎበታል፣ በነገርህ ላይ ይህ የራሴ አገላለጽ እንጂ ትክክለኛ ትርጉሙን ለማወቅ ከፈለግክ ከኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 3 ከ 1-3 በማንበብ የበለጠ መረዳት ትችላለህ፣ በዚህም መሰረት በሃገር ዉስጥም ሆነ በዉጪ መንግስታዊ ተቋማት በክብር እየተሰቀለ የሚዉለበለብ ሲሆን መለወጥ የሚችለዉም በዘፈቀደ ሳይሆን ህግና ስርዓት ተከትሎ በፓርላማና ምናልባትም ከህገ- መንግስቱ ጋር እንጂ በማንም ስሜተኛና ግንፍልተኛ የሚወርድና የሚንጠለጠል አይደለም፣ በመሆኑም መንግስት እነኝህን ጀብደኛ ወንጀለኞች በብሄራዊና ዓለም አቀፍ ህግ መሰረት ለፍትህ እንዲቀርቡና ተመጣጣኝ ፍርድ እንዲሰጣቸዉ ማድረግ አለበት፣ የኢትዮጵያ ህዝብም ዉጤቱን በጉጉት እየጠበቀ ነዉ።



ኢ.ህዴግ ስልጣን እንደያዘ ሻዕቢ.ያ በሃገራችን ላይ እንዴት ፈንጥዞ ዕንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነዉ፣ ቡና ሳይቀር ልውጭ ገበያ አቀረበ፣ የገበሬዉን የምርት ዉጤት በግዳጅና በሃስት ገንዘብ እየገዛ ወይም እየቀማ ልበለዉ ህዝባችንን አሰቃዬ፣ ብለን ያኔ በመንግስት ላይ በጋራ የጮህነዉን አትዘነጋዉም ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፣ መንግስት የህዝቡን ብሶት ሰምቶና ተረድቶ የምናዉቀዉን እርምጃ ሲወስድ ማነዉ ዛሬ ከሻዕቢ.ያ ጫማ ስር የወደቀው እነ ግንቦትና ሌሎች የህዝብ ጠላቶች አስመራ ተጠቃለዉ በመግባት በሃገር ዉስጥ ካለዉ አመራር እከሌ በግማሹ ኤርትራዊ ነው ሲሉ በዕውነት አያሳፍርም ጋናን አሁን ላለችበት ያበቋት መቶ አለቃ ጀሪ ሮውሊንግ በግማሽ ግሪካዊ፣ ፔሩን ወደ ዲሞክራሲ የመሯት ፉጂ ሞሪ ደግሞ ፣ በግማሽ ጃፓናዊ ናቸው ፣ ከ 11 ዙር ጦርነት በኋላ ክሪምን ከቱርክ የነጠቀችዉ የራሽያ ንግስት ታላቋ ካተሪና ጀርመናዊት እንደሆነች ላስታዉስህ ዕወዳለሁ። የዜግነትን ደረጃ ለመወሰን እኔም ሆንኩ አንተ ወይም ሌላ ማንም የሞራልም ሆነ ህጋዊ መብት የለንም፣ ናችው ቢባል እንኳ መመዘን የሚገባቸዉ እንደሌላዉ ሁሉ በተግባራቸው እንጂ የዘር ፖለቲካ እንቃወማለን እየተባለ ዋና ተዋናይ መሆን ዓላማን የሚጻረር ከመሆኑም በላይ በመጨረሻም ሰብዓዊና ፖለቲካዊ ቅሌትን ያስከትላል።

ሃገርን ለመምራት መጠን የሌለዉ ትዕግስት ያስፈልጋል፣ በዜግነት ለማገልገል ደግሞ የበለጠ መስዋዕትነት ይጠይቃል፣ የሆነው ጫና ይድረስባቸዉ ወይም በደል ይፈጸምባቸው ሃላፊነት የሚሰማቸዉ ሁሉ ለሃገራቸው ሲሉ ሁሌ ይቅር ባይ ናቸው ፣በተቃዋሚነትም ሆነ በተለያዬ ምክንያት ለዓመታት የታሰሩ የቁም ዕስር የነበሩና ከዚ.ያም አልፎ በስደት እየኖሩ በሃገራቸው ዕርቀ-ሰላም መረጋጋትና የጋራ እድገት እንዲኖር ምሳሌ የሆኑ ታላላቅ ተክለ-ሰዉነቶችን መጥቀስይቻላል፣ የቻይናው ዳላይ ላማ የበርማዋ ሳንሱቺ ወዘተ ሌላው ቀርቶ ከ 20 አመት በላይ ከቱርክ መንግስት ጋር በመዋጋት ለብዙ ሺሕ ህዝብ ህይዎት ማለፍ ምክንያት የሆነዉ የኩርዶች መሪ አብዱላ ኦቻላን ዛሬ አብሮ መኖርና መቻቻልን እየሰበከ ቀሪ ደፈጣ ተዋጊዎችን ከመንግስት ጋር በማግባባት ላይ ይገኛል፣በነገርህ ላይ ይህ ግለሰብ በ1990ዎች ናይሮቢ-ኬንያ በቱርክ የጸጥታ ሃይሎች ተይዞ ነው እስከዛሬ ድረስ ጥቁር ባህር ደሴት ላይ ብቻዉን ታስሮ የሚገኘዉ ። የኢሳት ባልደረቦችና የግንቦት 7 መሪ ግን ሃገር ቤት እያሉ በጋዜጠኝነት ስምና በተቃዋሚነት የቻሉትን ያህል ከለፈለፉና ከዘባረቁ በኋላ ሙያቸዉና ዓላማቸዉ ውጤት- አልባ ሲሆንባቸዉ አዉሮፓና አሜሪካ መሽገዉ በሚዘላብዱት ወሬ ኪሳቸዉን እያዳበሩ እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነዉ ከኤርትራና ከሌላ የሚደረግላቸዉ ድጎማና ዕርዳታ ሳይጨመር ማለት ነዉ፣ ይህም ብቻ አይደለም፣ ነጻ ሜዲያ ነን እያሉ እነሱን የሚደግፍ ካልሆነ እንኳን በጣቢያቸዉ በሌላ ድህረ-ገጽም ቢሆን አሉታን ያዘለ አስተያየትም ሆነ ጽሁፍ እንዳይወጣ ወይም እንዲነሳ ለማድረግ እጃቸዉን ማስረዘም ጀምረዋል ፣ ባለፈው ጊዜ ኤልያስ ክፍሌ በኢትዮሜዲያ ያሰፈረዉ ጽሁፍ ባስቸኳይ እንዲነሳ የተደረገው በኢሳትና ግንቦት 7 ከፍተኛ ተቃዉሞ እንደሆነ ልብ ይሏል።

ዉድ ጓደኛዬ

ከጥቂት ወራት በፊት ከ 30 የማይበልጡ ግልፍተኞች በሰላማዊ ሰልፍ ስም በከተማዉ ጠርዝ በሰፈሩ ወቅት „ ጓደኛው ቢ.ያሸንፈው ወደ ሚስቱ ሮጠ!“ እንደሚባለው መንግስትን ማሳመን የሚችል ፍሬ ሃሳብ ማቅረብ ሲ.ሳናቸዉ እኔንና ሌሎች ሃገር ወዳዶችን „ የኢ.ህዴግ ሰላዮች „ የሚል ስያሜ የተለጠፈበት ወረቀት ሲበትኑ እንደዋሉ ነግረሀኛል፣ ከሁሉም በላይ በጣም የገረመኝና ያሳዘነኝ

የተበተነውን ስም ዝርዝር ቤትህ ዉስጥ አስቀምጠህ ልትሰጠኝም ሆነ ልታሳየኝ ፈቃደኛ አለመሆንህ ነዉ፣ እንደሚመስለኝ በአንድ

በኩል ህጋዊ ጥያቄ ያስከትላል ከሚል ስጋት ሲሆን ሌላው ደግሞ ምናልባት የአንተ እጅ ይኖርበት ይሆን! ሁሉንም ጊዜ ያሳየናል፣ ዕውነቱን ልንገርህና ከቤትህ የወጣሁት ህሊናዬ ለሁለት ተከፍሎ ነዉ ፣ እኔን የጥንት ጓደኛህን አሁን ባገኘሃቸው ጋጠ ወጦች ትለዉጠኛለህ ብዬ እንዴት ላስብ! ጓደኝነት ያለዉን ዋጋ በሚገባ አዉቃለሁ ለዚህም ነዉ እስካሁን ድረስ አሽሙርና ሽሙጥ እየቻልኩ ለግንኙነታችን ትልቅ ዋጋ የሰጠሁት፣ የታገስኩት፣ ለዚህም ነው በዚህ አጭር መልዕክቴ ያለፍንበትን ያለንበትንና የወደፊቱን በተመለከተ የተሰማኝንና የማምንበትን የጻፍኩልህ፣ ገንቢና አስተማሪ የሆነ ዓጻፋ ከአንተ ባገኝ ደስታዉን አልችለዉም፣ በበኩሌ እንደጀመርኩት ሁሉ ለሃገሬ ወደፊትም አቅሜ የፈቀደዉን ከማድረግ ወደኋላ እንደማልል በዚህ አጋጣሚ አረጋግጥልሃለሁ፣በሃገሬ የምለውጠዉ ምንም የለኝም፣ ከማንም በላይ ሃገሬን እመርጣለሁ።

ያንተው ሚዛኑ ዓየለ ነኝ

amizanu@yahoo.de

የጣሉሽ ይውደቁ